እግዚአብሔር ግን ልጅ ሰጣት።

- እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር ማድረግ ይችላል።

- ለእግዚአብሔር የሚሳነው አንድም ነገር የለም።

- ከዚያስ ማርያም ምን አለች?

ሉቃስ 1፡38

38- ማርያምም «እነሆ፤ እኔ የጌታ ባሪያ ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» አለች። ከዚያም መልአኩ ተለይቶአት ሄደ።

- ማርያም በእግዚአብሔር ስላመነች፣ ለሚመጣው አዳኝ ለኢየሱስ እናት ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር መረጣት።

- ኢየሱስ ቃል የተገባው አዳኝ ነበር?

- አዎን።

- ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ከመጀመሪያው በዔድን የአትክልት ስፍራ ለአዳምና ለሔዋን ቃል የገባላቸው አዳኝ ነው?

- አዎን።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብና ለሰዎች ሁሉ ቃል የገባው አዳኝ ነው?

- አዎን።



## ትምህርት 43

1. እግዚአብሔር አሥሩን የእስራኤል ነገዶች እንዴት ቀጣቸው።

ሀ- እግዚአብሔር አሦራውያንን ልኮ ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች አሸንፈው ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው አደረገ።

2. እግዚአብሔር አሥሩን የእስራኤል ነገዶች ከቀጣቸው በኋላ፣ በይሁዳ ያሉትን ሁለቱን ነገዶች እንዴት ቀጣቸው።

ሀ- እግዚአብሔር ባቢሎናውያንን ልኮ በይሁዳ ያሉትን ሁለቱን ነገዶች አሸንፈው ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው አደረገ።

3. ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ከተማ የደመሰሱት እንዴት ነበር?

ሀ- ቤተ መቅደሱን በእሳት አቃጠሉ።

ለ- የኢየሩሳሌምን ከተማ በሙሉ አቃጠሉ።

ሐ- በከተማይቱ ዙርያ ያለውን ቅጥር አፈረሱ።

4. የይሁዳ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሱ ጊዜ ምን አደረጉ?

ሀ- ቤተ መቅደሱን እንደ ገና ሰሩ።

ለ- የኢየሩሳሌምን ከተማ እንደ ገና ሰሩ።

ሐ- በኢየሩሳሌም ከተማ ዙርያ ያለውን ቅጥር እንደገና ሰሩ።

5. ወደ ኢየሩሳሌም ለተመለሱት የይሁዳ ሰዎች የተሰጠው አዲሱ ስም ምን የሚል ነበር?

ሀ- አይሁድ።

6. እግዚአብሔር አይሁዶችን እንዲገዙ የላካቸው ሌሎች ሁለት ሕዝቦች እነማን ነበሩ።

ሀ- ግሪኮችና ሮማውያን።

7. ሮማውያን ማንን ያመልኩ ነበር?

ሀ- ብዙ ምስሎችን ያመልኩ ነበር።

ለ- ንጉሣቸውን ቄሳርንም ያመልኩ ነበር።

8. ጻፎች እነማን ነበሩ?

ሀ- ጻፎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚጽፉ የአይሁድ መሪዎች ነበሩ።

9. ፈሪሳውያን እነማን ነበሩ?

ሀ- ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ የአይሁድ መሪዎች ነበሩ።

10. ሰዱቃውያን እነማን ነበሩ?

ሀ- ሰዱቃውያን ሀብታሞችና የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች የሆኑ የአይሁድ መሪዎች ነበሩ።

11. ምኩራቦች ምንድን ናቸው?

ሀ- ምኩራቦች አይሁዶች የሙሴን መጽሐፎች ለማንበብና ለመወያየት የሚሰበሰቡባቸው ቤቶች ነበሩ።

12. በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ያመኑ አይሁዶች ነበሩ?

ሀ- አዎን፣

ለ- በእግዚአብሔር ያመኑ ጥቂት አይሁዶች ነበሩ።

- እግዚአብሔር መልእክቱን ለአይሁድ እንዲነግሩ ብዙ ነቢያትን ላከ።

- እግዚአብሔር ከላካቸው ከመጨረሻዎቹ ነቢያት አንዱ ሚልክያስ ነበር።



እንደምትፀንስ ነገራት።

- የማርያም ልጅ የሚወለደው ያለ ሰው አባትና እናት የዘር ፍሬ ነው።

- የማርያም ልጅ ያለ ሰው አባትና እናት የዘር ፍሬ የተወለደው ለምን ነበር?

- የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ሳይኖርበት እንዲወለድ።

- ያለ ኃጢአት ፍጹም ሆኖ እንዲወለድ።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ወልድ ያለ ኃጢአት ሆኖ ይወለድ ዘንድ፣ የሰው አባትም ሆነ እናት የዘር ፍሬ ስለማያስፈልገው ነው።

- የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ዘር ብቻ ይኖረዋል።

- ቀጥሎስ መልአኩ ማርያምን ምን አላት?

ሉቃስ 1፡36-37

36- መልአኩ እንዲህ አለ «እነሆ፤ ዘመድሽ ኤልሳቤጥም በስተ
እርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፤ መካን የተባለችውም ስድስተኛ ወሯን
ይዛለች፤
37- ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።»

- መልአኩ ማርያምን እንዲህ አላት፡

- ኤልሳቤጥ በጣም ያረጀችና መካን ሴት ስለሆነች ልጅ መውለድ አትችልም ነበር እግዚአብሔር ግን ልጅ ሰጥቷታል።

- እንደዚሁም ማርያም ድንግል ስለሆነች ልጅ መውለድ ባትችልም

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ለዳዊት አዳኙ ከእርሱ ትውልድ አንዱ እንደሚሆን ቃል ስለገባለት ነው።

- ምክንያቱም አዳኙ ከንጉሥ ዳዊት ዘር ስለሚመጣ፣ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ለዘላለም ያነግሠዋል።

- ማርያም መልአኩን ምን ብላ ጠየቀችው?

ሉቃስ 1፡34

34- ማርያም መልአኩን፣ «እኔ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?» አለችው።

- የማርያም ጥያቄ ምን ነበር?
- ማርያም ድንግል ሆና እንዴት ልጅ መውለድ እንደምትችል ጠየቀችው።

- መልአኩ ምን መለሰላት?

ሉቃስ 1፡35

35- መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፤ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ የሚወለደው ቅዱሱ ሕፃን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።»

- መልአኩ ምን አላት?

- መልአኩ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተአምር እንደሚሠራና ማርያም



- ሚልክያስ እግዚአብሔር አይሁዶችን እንዳልረሳቸውና አዳኝ እንደሚልክላቸው ነገራቸው።

- ሚልክያስ ከሞተ በኋላ ለ400 ዓመታት እግዚአብሔር ለአይሁዶች አልተናገረም።

- አብዛኞዎቹ አይሁዶች በእግዚአብሔር በማያምኑበት ወቅት ጥቂቶቹ ግን አዳኝ እስኪልክላቸው ድረስ እግዚአብሔርን ይጠባበቁ ነበር።

- እግዚአብሔር አዳኝ እስኪልክላቸው ድረስ ከሚጠብቁት አይሁዶች መካከል ሁለቱ ዘካርያስና ሚስቱ ኤልሳቤጥ ነበሩ።

ሉቃስ 1፡5-6

5- በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን፣ ከአብያ የክህነት ምድብ የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ፣ ሚስቱ ኤልሳቤጥም ከአሮን ነገድ ነበረች።
6- ሁለቱም የጌታን ትእዛዝና ሥርዓት ሁሉ ጠብቀው ያለ ነቀፋ የሚኖሩ፣ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ።

- ዘካሪያስ ካህን ነበረ ዘካርያስና ሚስቱ በእግዚአብሔር ያምኑ ነበር።
- ነገር ግን ዘካርያስና ሚስቱ ችግር ነበረባቸው።

ሉቃስ 1፡7

7- ይሁን እንጂ ኤልሳቤጥ መካን በመሆኗ ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜ የገፉ ነበሩ።

- የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ችግር ምን ነበር?

- ልጅ አልወለዱም ነበር።

- ልጅ ያልወለዱት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኤልሳቤጥ መካን ስለ ነበረች ነው።

- ምክንያቱም ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ሁለቱም በጣም አርጅተው ስለ ነበር ነው።

- ዘካርያስ ካህን ስለ ነበረ፣ ሥራው በቤተ መቅደስ ውስጥ ማገልገል ነበር።

ሉቃስ 1፡8-10

8- አንድ ቀን ዘካርያስ በምድቡ ተራ፣ በእግዚአብሔር ፊት በክህነት በሚያገለግልበት ጊዜ፣

9- በሥርዓተ ክህነቱ መሰረት፣ ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን በዕጣ ተመረጠ።

10- ዕጣን በሚታጠንበትም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ሆኖ ይጸልይ ነበር።

- ዘካርያስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ ለእግዚአብሔር በሚያጥንበት ጊዜ አንድ ነገር ሆነ።

- ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለ ምን ሆነ?

- የእግዚአብሔር መልአክ ለዘካርያስ ተገለጠለት።



- እግዚአብሔር ልጅ ወልዷል?

- አልወለደም።

- እግዚአብሔር አንድ ሆኖ በአካል ሦስት ስለ መሆኑ ታስታውሳላችሁ?

- እግዚአብሔር እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

- እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድን እንደ እግዚአብሔር ልጅና እንደ ሰው ልጅ ወደ ምድር ላኩት።

- የማርያም ልጅ አምላክ ወይስ ሰው ነው?

- የማርያም ልጅ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው።

- መልአኩ ስለ ማርያም ልጅ፥ ስለ ሚመጣው አዳኝ ሌላ ምን አለ?

ሉቃስ 1፡32ለ-33

32- መልአኩ እንዲህ አለ «ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤

33- በያዕቆብም ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም። »

- መልአኩ የማርያም ልጅ መጪው አዳኝ የዳዊት ዘር እንደሚሆን ተናገረ።

- አዳኝ ከዳዊት የዘር ግንድ የሚወለደው ለምንድን ነው?

- ማርያም እንደ ማንኛውም ሰው በኃጢአት አልተወለደችምን?
- ተወልዳለች።

- ታዲያ እግዚአብሔር ማርያምን ለምን መረጣት?

- ምክንያቱም ማርያም በእግዚአብሔር ታምን ስለ ነበር ነው።

- ምክንያቱም ማርያም እግዚአብሔርን አዳኝ እንደሚልክ ትጠባበቅ ስለ ነበር ነው።

- የማርያም ልጅ ስሙ ማን ይባላል?
- ኢየሱስ።

- «ኢየሱስ» ማለት ምን ማለት ነው?
- «ኢየሱስ» ማለት አዳኝ ወይም ታዳጊ ማለት ነው።

- መልአኩ ስለ ማርያም ልጅ፥ ስለሚመጣው አዳኝ ምን አለ?

ሉቃስ 1፡32ሀ

32- መልአኩ እንዲህ አለ «እርሱም ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም ይባላል።»

- መልአኩ የማርያም ልጅ የልዑል ልጅ እንደሚባል ተናገረ።
- መልአኩ የማርያም ልጅ የልዑል ልጅ ይባላል ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለቱ ነው።
- የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆነው እንዴት ነው።



ሉቃስ 1፡11-14

11- የጌታም መልአክ ከዕጣን መሰዊያው በስተ ቀኝ ቆሞ ታየው።
12- ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፤ በፍርሀትም ተዋጠ።
13- መልአኩ ግን እንዲህ አለው፤ «ዘካርያስ ሆይ፤ አትፍራ፤
ጸሎትህ ተሰምቶአል፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤
ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።
14- በእርሱ ተድላና ደስታ ታገኛለህ፤ ብዙዎችም እርሱ በመወለዱ
ደስ ይላቸዋል።»

- መልአኩ ዘካርያስን ምን አለው?

- መልአኩ እግዚአብሔር ለዘካርያስ ልጅ እንደሚሰጠውና የልጁም ስም ዮሐንስ እንደሚባል ነገረው።

- ቀጥሎስ መልአኩ እግዚአብሔር ለዘካርያስ ስለሚሰጠው ልጅ ምን አለ?

ሉቃስ 1፡15-17

15- «በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና። የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ
የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ በእናቱም ማሕፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ
ይሞላል።
16- ከእስራኤልም ሰዎች ብዙዎቹን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው
ይመልሳቸዋል፤
17- የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው፣ የማይታዘዙትንም ወደ
ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ፣ ለጌታ የተገባ ሕዝብ ለማዘጋጀት በኤልያስ
መንፈስና ኀይል በጌታ ፊት ይሄዳል።»

- መልአኩ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ሕዝቡን ለሚመጣው አዳኝ ያዘጋጃል አለ።

- መልአኩ የሚመጣውን አዳኝ ማን አለው?
- ጌታ።
- ጌታ ማን ነው?
- እግዚአብሔር።

- መልአኩ የሚመጣው አዳኝ ጌታ እግዚአብሔር ራሱ ነው አለ።

- ከዚህ በኋላ የዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ ጸነሰች።

ሉቃስ 1፥24-25

24- ከዚህ በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ፀነሰች። አምስት ወራትም ራሷን ሰወረች፤

25- እርሷም፣ «ጌታ በምሕረቱ ነቀፌታዬን ከሰው መካከል ሊያስወግድልኝ ተመልክቶ በዚህ ጊዜ ይህን አድርጎልኛል» አለች።

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር መልአኩን ማርያም ወደምትባል ወደ አንዲት ድንግል ላከ።

ሉቃስ 1፥26-31

26- በስድስተኛው ወር እግዚአብሔር መልአኩ ገብርኤልን በገሊላ ወደምትገኘው ወደ ናዝሬት ከተማ ላከው፤

27- የተላከውም ከዳዊት ዘር ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ነበር፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበር።



28- መልአኩም እርሷ ወዳለችበት ገብቶ፤ «እጅግ የተወደድሽ ሆይ፣ ሰላም ለአንቺ ይሁን፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ የተባረክሽ ነሽ» አላት።

29- ማርያምም በንግግሩ እጅግ በጣም ደንግጣ፣ «ይህ ምን ዓይነት ሰላምታ ይሆን?» እያለች ነገሩን ታሰላስል ጀመር፤

30- መልአኩም እንዲህ አላት፤ «ማርያም ሆይ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ።

31- እነሆ፣ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።»

- መልአኩ ለማርያምን ምን ነገራት?

- መልአኩ ማርያም የሚመጣውን አዳኝ እንድትወልድ እግዚአብሔር እንደ መረጣት ነገራት።

- እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል ረስቶአል?
- አልረሳም።

- እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል ያስታወሰው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለሚወድ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ከኃጢአት፣ ከሞትና ከሰይጣን ለማዳን ስለሚፈልግ ነው።

- እግዚአብሔር ማርያምን ለምን መረጣት?

- ማርያም የአዳምና የሔዋን ዘር አይደለችምን?
- ናት።